


www.oref.org.il



በሚሳይል ተኩስ ጊዜ ቤተሰቤ የሚያደርጋቸው ዝግጅቶች

ፒ.ሲ.ኦ 1457



የሀዝብ ደጀን



104

ሁላችንም ኃላፊነት አንወስዳለን

የሲቪል አስተዳደር

ውድ ኗሪዎች

በዚህ በራሪ ወረቀት ውስጥ ወደ መሸሸጊያ ክፍል የምትገቡበትን ሰዓት እንደዚህም ራሳችሁን ለመከላከል እንድትዘጋጁ የሚረዷችሁን የተወሰኑ ቀለል ያሉ መመሪያዎችንና እርምጃዎችን በዝርዝር እናቀርባለን። እነዚህም፡-

- የመሸሸጊያ ክፍል አመራረጥ መመሪያዎች
- የማስጠንቀቂያ ደወል ሲሰማ መደረግ ያለባቸው ነገሮች መመሪያ
- ቤተሰባዊ የአደጋ ጊዜ ዕቅድ
- የመከላከያ አካባቢዎች ካርታ በአዲሱ የመግቢያ ሰዓት መሠረት ከናንተ ጋር፣ የህዝብ ደጀን ("ፒኩድ ሃየሬፍ")

የመሸሸጊያ ክፍል አመራረጥና አዘገጃጀት መመሪያዎች
የማስጠንቀቂያ ደወል ወይም የፍንዳታ ድምጽ ሲሰማ ያለንን ጊዜ ላይ በመጠቀም የመሸሸጊያ ክፍሉን በሚከተለው ቅደም ተከተል መሠረት መምረጥ ያስፈልጋል።

የሕንጻ ውስጥ የመሸሸጊያ ክፍል (ד"ממ) ወይም **የፎቅ ላይ መሸሸጊያ ክፍል (ק"ממ)** ተመራጭነት አላቸው።

ሚቅላጥ፣

በጋራ ሕንጻ ውስጥ የሚገኝ ሚቅላጥ፣ ውስጣዊ ሚቅላጥ ሕንጻው ውስጥ የሚገኝ ከሆነና ማስጠንቀቂያ በተሰጠበት ጊዜ ሳይወሰን ወደ ሚቅላጡ በውስጣዊ ደረጃዎች አማካይነት መድረስ የሚቻል ከሆነ

በጋራ ሕንጻ ውስጥ የሚገኝ ሚቅላጥ፣ ወደ ሚቅላጡ የማስጠንቀቂያ ደወል እንደተሰማ በተወሰነ ጊዜ መድረስ የሚቻል ከሆነ።

ባለችሁበት ቦታ የሕንጻ ውስጥ የመሸሸጊያ ክፍል (ד"ממ)፣ የፎቅ ላይ መሸሸጊያ ክፍል (ק"ממ) ወይም ሚቅላጥ ከሌለ፣ በጣም ጥቂት ውጫዊ ግድግዳዎች፣ መስኮቶችና ክፍተቶች ያሉበትን **ውስጣዊ የመሸሸጊያ ክፍል** መምረጥ ያስፈልጋል።

የሕንጻ ውስጥ የመሸሸጊያ ክፍል (ד"ממ)፣ የፎቅ ላይ መሸሸጊያ ክፍል (ק"ממ) ወይም ሚቅላጥ በሌለው **ከ3 ፎቆች በላይ ባሉት ሕንጻ** በላይኛው ፎቅ ላይ የሚኖሩ ከቤታቸው በታች ሁለት ፎቆች ወደታች በመውረድ በፎቁ ደረጃዎች ላይ መቆየት አለባቸው።

የሕንጻ ውስጥ የመሸሸጊያ ክፍል (ד"ממ)፣ የፎቅ ላይ መሸሸጊያ ክፍል (ק"ממ) ወይም ሚቅላጥ በሌለው **እስከ3 ፎቆች ባሉት ሕንጻ** በላይኛው ፎቅ ላይ የሚኖሩ ከቤታቸው በታች አንድ ፎቅ ወደታች በመውረድ በፎቁ ደረጃዎች ላይ መቆየት አለባቸው።

የማስጠንቀቂያ ደወል ሲሰማ የሚደረጉ መመሪያዎች
የማስጠንቀቂያ ደወል ወይም የፈንጅ ድምጽ በተሰማ ጊዜ ወደ መሸሸጊያ ክፍል ባለን የጊዜ ገደብ ውስጥ ለመግባት የሚቀጥሉትን መመሪያዎች በመከተል ይሆናል፣

1. **በሕንጻ ውስጥ ያሉ፣** በፍጥነት ወደ ሕንጻው መሸሸጊያ ክፍል (ד"ממ) ግቡና – የብረቱን መስኮት ዝጉ። በሕንጻው ውስጥ የመሸሸጊያ ክፍል (ד"ממ) ከሌለ በጣም ጥቂት ውጫዊ ግድግዳዎች፣ መስኮቶችና ክፍተቶች ወዳሉበት ክፍል መግባት ያስፈልጋል። የዚህ ዓይነት ክፍል ከሌለ ወደሕንጻው ደረጃዎች ወጥቶ መቀመጥ ያስፈልጋል። በሕንጻው መሸሸጊያ ክፍል (ד"ממ) ወለል ላይ ከመስኮቱ በታች ተቀመጡ። ከመስኮቱ ፊት ለፊት አትቀመጡ።
2. **ከሕንጻ ውጪ የምትገኙ ከሆነ፣ ወደሕንጻው ወይም ሌላ በአቅራቢያው ወደሚገኝ መሸሸጊያ ግቡ።** ሜዳ ላይ ከሆናችሁ – መሬት ላይ ተጋደሙና ራሳችሁ እንዳይጐዳ/እንዳይመታ በእጃችሁ ሸፍናችሁ ያዙት።
3. **በተሸከርካሪ/በመኪና ለምትጓዙ፣ መንገድ ዳር ተሸከርካሪውን ካቆማችሁ በኋላ በአካባቢው ሕንጻ ወይም መሸሸጊያ ቦታ ካለ ወደዚያ ግቡ።** ከመኪናው ውስጥ ባለን የጊዜ ገደብ ውስጥ በአካባቢው ሕንጻ ወይም መሸሸጊያ ቦታ መድረስ የማይቻል ከሆነ መኪናውን በመንገድ ዳር በማቆም መሬት ላይ ተጋደሙና ራሳችሁ እንዳይጐዳ/እንዳይመታ በእጃችሁ ሸፍናችሁ ያዙት።
4. **ከ10 ደቂቃዎች በኋላ፣ ተጨማሪ የማስጠንቀቂያ ድምጽ ወይም ሌላ መመሪያ እስካልተሰጠ ድረስ ከመሸሸጊያው ክፍል መውጣት ይቻላል።**
5. **ከአጠራጣሪና ወድቀው ከሚገኙ ነገሮች አንደዚሁም ወድቆ ከሚገኝ ሮኬት ራቁ።** የዚህ ዓይነት ሁኔታ ሲያጋጥም ተመልካቾችን ከቦታው በማራቅ ለፖሊስ ማስታወቅ ያስፈልጋል።



ቤተሰባዊ የድንገተኛ ጊዜ ፕሮግራም ማዘጋጀት
ቤተሰብ ለወላጆች ሆነ ለልጆች ዋናው ድጋፍ ሰጪ አካል ነው። በመሆኑም ሁሉም የቤተሰቡ አባላት በዝግጅቱ ላይ ተሳታፊ መሆን አለባቸው። ይህም በተለያዩ ሁኔታዎች ችግሮችን በጥሩ ሁኔታ አንዲጋፈጡ ያስችላቸዋል።

1. **ሁሉም የቤተሰቡ አባላት፣** ልጆችን ጨምሮ፣ **በማስጠንቀቂያ ደወል ጊዜ መመሪያዎችን አንዲያውቁ** ማድረግ ያስፈልጋል። ይህም ምን ማድረግ እንደሚገባቸውና በቤት ውስጥ በሌሉበት ጊዜ ወይም ብቻቸውን ሲሆኑ ወዴት መግባት እንዳለባቸው እንዲያውቁ ይረዳቸዋል።
2. በማስጠንቀቂያው ደወል ጊዜ የምትገቡበትን **የመሸሸጊያ ክፍል** ከልጆችና ከቤተሰቡ አባላት ጋር በአንድነት በመሆን ምረጡ። ክፍሉ የተመረጠበትንም ምክንያት አስረዱ። (ማለትም ለምን ይህ በቤቱ ውስጥ ጥሩ መመሸጊያ ክፍል እንደሆነና ለምን በማስጠንቀቂያው ደወል ጊዜ ወደዚህ ክፍል መግባት አስፈላጊ እንደሆነ በደንብ አብራሩ)።
3. በቤተሰቡ አባላት መካከል **የሥራ ክፍፍሎችን አድርጉ።** በተጨማሪም በቤተሰባችሁ ልዩ ፍላጐት መሠረት ዝግጅት አድርጉ።
4. በችግር ጊዜ በጥሩ ሁኔታ ለመጋፈጥ **ሊረዷችሁ የሚችሉ ነገሮችን ያዙ።** ይህም ጥቂት ውሃና ምግብ፣ የድንገተኛ ሁኔታ ጊዜ መብራት፣ ራዲዮ ከባትሪ ድንጋይ ጋር እና የመጀመሪያ የሕክምና እርዳታ መሣሪያዎች።
5. ልጆቻሁ ሆነ ሌሎቹ የቤተሰብ አባላት በተለያዩ ሁኔታዎች ጊዜ ለማን መደወል እንደሚገባቸው ሊያዝ የሚችሉ **የስልክ ቁጥር ዝርዝሮችን አዘጋጁ።** በዚህም መሠረት የእሰራኤል ፖሊስ፣ የማጌን ዳቪድ አዶም፣ የእሳት መከላከያና ማዋሪያ፣ የሲቪል አስተዳደር፣ የሥራ ቦታችሁን ስልክ ቁጥሮችና የእጅ ስልክ ቁጥሮችን መዝግቡ።
6. ሚሳይል ወይም ሮኬቶች ቢተኮሱ ምን ማድረግ እንዳለባችሁ **ከቤተሰቦቻችሁ አባላት ጋር ተነጋገሩ።** ውይይቱን ወላጅ እየመራ ልጆች ደግሞ በውይይቱ ላይ ተሳታፊ እንዲሆኑ ያስፈልጋል። ከሁኔታው የተነሣ አንዱ ወላጅ ጭንቀት ቢሰማው ውይይቱን መምራት አያስፈልገውም። በዚህም ፋንታ ልጆቹ ወደሚማሩበት ት/ቤት በማመልከት ውይይቱን እንዴት መምራት እንዳለበት መመሪያዎችን መቀበል አለበት። ከውይይቱ በፊት ራስን ማዘጋጀት ያስፈልጋል።

- የውይይቱ ርእሶች ምን መሆን እንዳለባቸው አስቡ
- ውይይቱን ለማድረግ ጊዜ መድቡ እንደዚሁም ለሁላችሁም ተስማሚ የሆነ ቦታ ወስኑ
- በ2ኛው የሊባኖስ ጦርነት ጊዜና በተለያዩ ፍልሚያዎች ጊዜ በጋዛ ዙሪያ የሚገኙ መንደር ኗሪዎች ሕይወት የዳነው ለመመሪያዎቹ በመታዘዛቸው መሆኑን ለልጆቻችሁ አስረዱ። ልጆቻችሁም ስለተሰማቸው ነገር እንዲናገሩ ዕድል ስጧቸው።

ከጐረቤቶቻችሁ ጋር መተባበርና እርስ በርስ መረዳዳት ታላቅ ጠቃሚነት አለው። ስለዚህ ከጐረቤቶቻችሁ ጋር ስለአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታዎች ተወያዩ፣ እንደዚሁም ማድረግ ስለሚገባችሁ ነገር ወስኑ።



የህዝብ ደጀን

የማስጠንቀቂያ ሥርዓቱ እንዲሻሻል ይሠራል። እንደዚሁም በአስቸኳይ ሁኔታዎች ጊዜ በክልላዊ ሬዲዮ ጣቢያዎች አማካይነት የማስጠንቀቂያ ደወሉን እንድትሰሙ ያስችላችኋል። የሬዲዮ ሞገዶቹ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ይገለጻሉ።

ተጨማሪ መረጃ የሲቪል አስተዳደር
("ፒኩድ ሀየሬፍ") ድረ - ገጽ ከሆነው

www.oref.org.il

ወይም በ ወይም ከመረጃ ማዕከሉ በስልክ ቁጥር **104** መቀበል ይቻላል።